# I. <u>መግቢያ</u>

የሰው ልጅ ክብር የተሞላበት ደረጃውን የጠበቀ ኑሮ እንዲኖር አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ የተሟላ መጠለያ /መኖሪያ ቤት/ የማግኘት መብት ነው፡፡ ይህም መብት እ.ኤ.አ በ1948 በወጣው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ሰነድ ላይ ተገቢው ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን ይህንኑ መግለጫ መሠረት በማድረግ በወጣው የኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳንና ሌሎች አስገዳጅ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ሠፍረው እናገኛለን፡፡

በዓለም አቀፉ የኢኮኖሚያዊ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 11 ላይም የመብቱ አጠባበቅ በሚከተለው መልኩ ተቀምጧል፡፡

> *«የዚህ ቃል ኪዳን ተዋዋይ አገሮች ማንኛውም ሰው በቂ ምግብ፣ ልብስና መኖሪያ ቤትን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ በቂ የሆነ የኑሮ ደረጃ ለመኖርና ኑሮውንም በየጊዜው ለማሻሻል መብት ያለው መሆኑን ዕውቅና ይሰጣሉ፡፡ አባል አገሮቹ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ዓለምአቀፍ ትብብርን አስፈላጊነት ተገንዝበው ይህንን መብት ሙሉ ለሙሉ በሥራ ለመተርጐም ተገቢውን ዕርምጃ ይወስዳሉ፡፡»*

እነዚህን ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች ያፀደቁና የተፈራረሙ አገሮችም ህገ-መንግስትን ጨምሮ በሚያወጧቸው አገር አቀፍ ህጎች የዜጎቻቸውን የተሟላ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብትን ለማስጠበቅ ግዴታ በመግባት ስምምነቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

# II. <u>የተሟላ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ስንል ምን ማለታችን ነው?</u>

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችን በተመለከተ ማብራሪያ የሚሠጠው ኮሚቴ ጠቃላይ ትንታኔው (General Comment) ቁጥር 4 ላይ የተሟላ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት ምን ምን ሁኔታ ዎችን ማሟላት/ማካተት እንዳለበት እንደሚከተለው ዘርዝሯል፡፡

**1. <u>በህግ የተጠበቀ የይዞታ መብት</u> -** አንድ ሰው ቤ ትን በባለቤትነት፣ ከመንግስትም ሆነ ከግለሰቦች በመከራየት ወይም በሌላ ህጋዊ መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡ በመሆኑም በየትኛውም መልኩ የቤቱ ባለይዞታ የሆነ ሰው በኃይል ከመፈናቀል ወይም የይዞታ መብቱን በአግባቡ እንዳይጠቀም ከሚያደርጉ ተፅዕኖዎች ነፃ ሲሆን/ሲጠበቅ ይገባዋል፡፡

**2. <u>የቁሳቁሶች፣ የአገልግሎቶችና የመሠረት ልማት መኖር</u> -** ለጤና፣ ለፀጥታና ለምቾት እንዲሁም ለምግብ አቅርቦት አስፈላጊ የሆኑ ለምሳሌ የመጠጥ ውሃ፣ የንፅህና መጠበቂያ፣ ለማብሰያ ለማሞቂያና ለኃይል ማመንጫ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ለተሟላ የመኖሪያ ቤት ሊኖሩ የግድ ነው፡፡

**3. <u>አቅምን ያገናዘበ መሆን</u> -** በመኖሪያ ቤት ለመገልገል የሚውለው ወጪ የባለይዞታውን የገቢ መጠን ያገናዘበ መሆን የሚገባው ሲሆን ይህም ወጪ ባለይዞታው ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ፍላጎቶችን እንዳያሟላ ዕንቅፋት ሊሆንበት አይገባም፡፡

**4. <u>ለመኖሪያ ተስማሚ መሆን</u> -** የመኖሪያ ቤቱ በቂ የሆነ የቦታ ሥፋት ያለው እንዲሁም ብክለትን ከሚያመጡና ለጤና ጠንቅ ከሆኑ ነገሮች (ከብርድ፣ ከዝናብ እና ከንፋስ) ነፃ የሆነ መሆን አለበት፡፡



*የመኖሪያ ቤቶች ለኑሮ ምቹና ተስማሚ ሊሆኑ ይገባል!*

**5. <u>አቅርቦት</u> -** የተሟላ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ለሁሉም ሰው ክፍት ሊሆን የሚገባው ሲሆን መንግስትም እያንዳንዱ ሰው ደህንነቱና ክብሩ ተ ጠብቆ በሰላም በቤቱ ውስጥ እየኖረ መሆኑን የማ ረጋገጥ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

**6. <u>ቅርበት</u> -** አንድ የመኖሪያ ቤት የሥራ ዕድልን፣ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች በቅርብ ለማግኘት በሚያስችልና የተጋነነ የመጓጓዣ ወጪ በማያስከትል አቀማመጥ መገኘት ይኖርበታል፡፡

**7. <u>ባህላዊ ዕሴቶችን መጠበቅ</u> -** የመኖሪያ ቤቶቹ አሠራር የባህላዊ ማንነት መገለጫዎችን በሚያጠፋ መልኩ ሊሆን አይገባም፡፡

## III. <u>የመንግስት ግዴታዎች</u>

ዜጎች የተሟላ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብታቸውን በመጠበቅ ረገድ መንግስታት የተለያዩ ግዴታዎች እንዳሉባቸው በዓለም ዐቀፍ የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባሕላዊ ስምምነት ላይ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-



*ሁሉም ዜጎች የተሟላ የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት አላቸው*

ስምምነቱን ያፀደቁ መንግስታት የሀገራቸው ህጎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኙ መመዘኛ ዎችን/መሥፈርቶችን በመጠበቅ የተሟላ መኖሪያ ቤ ትን የሚመለከቱ ህጎችን እና ፖሊሲዎችን የማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፣

በግልም ሆነ በዓለም አቀፍ ዕርዳታና ትብብር አማካኝነት መብቱ መከበሩን የማረጋገጥ ይህም ማለት መንግስታት ሃገሮቻቸው ያላቸውን የሀብት መጠን በመጠቀም መብቱን የማስጠበቅ በቂ ሃብት ከሌለም የሌሎቹን ሃገራት ዕርዳታ በመጠየቅ መብቱን ለማሟላት ተገቢውን ጥረት ማድረግና፣ ዜጎች በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ እንዲኖሩ የሚያስችሉ አስፈላጊ ዕርምጃዎችን መውሰድ፣ የሚሉት ይገኙባቸዋል፡፡

ኢትዮጵያም ከላይ የተጠቀሰው የዓለም አቀፍ የኢኮሚያዊ፣ ማኀበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃልኪዳንን ተቀብላ የፈረመች በመሆኑ መንግስትም በስምምነቱ ላይ የተገለፁትን ግዴታዎች ሲወጣ የሚገባው ከመሆኑም በተጨማሪ ዜጎችም መብቱ እንዲሟላላቸው የመጠየቅ መብታቸውን ሊያከብር ይገባል፡፡

★★★

*ይህን አጭር ጽሁፍ ያዘጋጀው አክሽን የባለሙያ-ች ማህበር ለህዝብ (አፕአፕ) ነው፡፡ አፕአፕ በ1985 ዓ.ም የተቋቋመ አገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን የተቋቋመበትም አላማ ህግና ሰብአዊ መብትን በመጠቀም የድሆችን በተለይ የሴቶችና የህጻናትን ሰብአዊ መብቶችን ማስከበር ነው፡፡*

*ለበለጠ መረጃ ከታች በተቀመጠው አድራሻ ያነጋግሩን፡፡*

ስድስት ኪሎ፣ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል
በሚወስደው መንገድ ፤
ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን አለፍ ብሎ፣
አዲስ የተሰራው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ህንፃ ፊት ለፊት
ፖ.ሣ.ቁ. 12484፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-1-243555፣ፋክስ 251-11-1243558
ኢ-ሜይል፡apap@ethionet.et
ዌብ ሳይት(ድረ-ገፅ): **http:**\\www.apapeth.org

# የተሟላ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት

**አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለሕዝብ (አኘአኘ)**